BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## አዳዲስ ሰዎችን መተዋወቅ
## ስሜ እከሌ ይባላል

*This is not a word-for-word transcript.*

ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያጠናቸው የሚገቡ የቋንቋ መሠረታዊያንን ወደሚያስተምረው Essential English እንኳን በደህና መጡ። ሐና እባላለሁ። በዚህ ክፍል ራስዎን ማስተዋወቅን ይማራሉ።

ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ለመገንዘብ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገናኙ ሁለት ሰዎችን ያዳምጡ።

**Sian**
*Hello, I'm Sian. What's your name?*

**Phil**
*Hi. My name's Phil. Nice to meet you.*

**Sian**
*Nice to meet you, too!*

ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎ፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።

የመጀመሪያዋ ሴት ‘ሄሎ፣ ሻን እባላለሁ’ ‘Hello, I’m Sian’ ብላለች። እርስዎ ‘Hello, I’m….’ ብለው ከዚያ ስምዎትን ማስከተል ይችላሉ። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Hello, I'm Sian.*

. . . ከዚያም ሌላኛውን ሰው ‘ስምህ ማነው?’ ‘what’s your name?’ ስትል ትጠይቀዋለች። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*What's your name?*

ሁለተኛው ተናጋሪ ስሙን ለማስተዋወቅ የተጠቀመው ሌላ መንገድን ነው፤ ‘ስሜ እከሌ ይባላል’ ‘my name is’ ነው ያለው። ስምዎትን ለመጥቀስ ‘I’m…’ ወይንም ‘my name is…’ የሚሉትን ሐረጋት መጠቀም ይችላሉ። ለምሳሌ ‘I’m…’ ወይንም ‘My name is…’ ማለት ይችላሉ። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*My name's Phil.*

ፊል ስሙን ከተናገረ በኋላ ‘nice to meet you’ ሲል ጨምሮ ተናግሯል። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*Nice to meet you.*


© British Broadcasting Corporation 2018

ከዚያም ሻን ‘nice to meet you’ በማለት ከመለሰች በኋላ የሐረጉ መጨረሻ ላይ ‘too’ የሚል ቃል ጨምራለች፤ ይህም ለሌላኛው ሰው ተመሳሳይ ነገርን ስንመልስ የምንጠቀመው ነው። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*Nice to meet you, too.*

በጣም ጥሩ፤ አሁን ሌሎች ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኙ የተባባሉትን በማዳመጥ እርስዎ ካሉት ጋር ያመሳክሩ።

*Hi, I'm Pete. What's your name?*

*Hi, my name's Mark. Nice to meet you.*

*Nice to meet you, too!*

*Hi, I'm Alice. What's your name?*

*Hi, my name's Claire. Nice to meet you.*

*Nice to meet you, too!*

ይህንን ምሳሌ እንደገና እንሞክራለን። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዱን አረፍተ ነገር አንዳንድ ጊዜ ይሰሙታል።

*Hello, I'm Sian. What's your name?*

*Hi, my name's Phil. Nice to meet you.*

*Nice to meet you, too!*

በጣም ጥሩ! አሁን ደግሞ እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታውሱት እንመልከት። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጧቸውና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይናገሩ።

ሄሎ፥ ሻን እባላለሁ።

*Hello, I’m Sian.*

ስምህ ማነው?

*What’s your name?*

ሃይ፥ ስሜ ፊል ይባላል።

*Hi, my name’s Phil.*


© British Broadcasting Corporation 2018

ስላተዋወቅኩሽ ደስ ብሎኛል።

*Nice to meet you.*

እኔም ስላተዋወቁክህ ደስ ብሎኛል።

*Nice to meet you, too.*

በጣም ጥሩ አሁን ጠቅላላውን ውይይት እንደገና ያዳምጡ።

**Sian**
*Hello, I'm Sian. What's your name?*

**Phil**
*Hi, my name's Phil. Nice to meet you.*

**Sian**
*Nice to meet you, too!*

በጣም ጥሩ። አሁን በእንግሊዝኛ ስምዎትን መናገር እና የሌሎች ሰዎችን ስም መጠየቅ ይችላሉ። የተማሩትን ደጋግሞ መለማምድን ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና ስም መጠየቅና መናገርን ይለማመዱ። 'Nice to meet you!' ማለትንም ይጨምሩ። ለተጨማሪ የ Essential English ዝግጅቶች በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ደህና ይሁኑ!


© British Broadcasting Corporation 2018